የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 35
ADDIS ABABA - 29th June, 2001

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፺፫ ዓ·ም
የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሳቢ መለያ፣ መመርመሪያና
መመዝገቢያ (ማሻሻያ) ደንብ ....................... ገጽ ፩ሺ፭፻፴፰

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 74/2001
Motor Vehicles and Trailers Identification, Inspection and Registration (Amendment)
Regulations ................................................ Page 1538

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፺፫
### የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሳቢ መለያ መመርመሪያና
### መመዝገቢያ ማሻሻያ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሣቢ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሣቢ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ደንብ ቁጥር ፫፻፷/፲፱፻፷፩ (እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· "ሚኒስቴር" የሚለው ቃል ተሠርዞ "ባለሥልጣን" በሚለው ተተክቷል።

፪· የአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተተክቷል፤

"፲፪· "የመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአገር መከላከያ ኃይል ንብረት የሆነ ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ ነው።"

፫· የአንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፭) ተሰርዘዋል። ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነዋል።

፬· የአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፬) ተሰርዘዋል። ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፭) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆነዋል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No.74/2001
### MOTOR VEHICLES AND TRAILERS IDENTIFICATION, INSPECTION AND REGISTRATION (AMENDMENT) REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Motor Vehicles and Trailers Identification, Inspection and Registration (Amendment) Regulations No. 74/2001.

2. *Amendment*

   The Motor Vehicles and Trailers Identification, Inspection Registration Regulations No. 360/1969 (as amended) is hereby further amended as follows:

   1) The word "Ministry" is deleted and replaced by "Authority",
   2) Sub Article (12) of Article 3 is deleted and replaced by a the following new Sub Article (12):

      "12) "Defence Force Vehicle" shall mean any motor vehicle or trailer owned by the National Defence Force of the Federal Democratic Republic of Ethiopia."

   3) Sub Articles (3) and (5) of Article 6 are deleted. Sub-Articles (4) and (6) are re-numbered as Sub-Article (3) and 4 respectively.
   4) sub-Articles (2) and (4) of Article 13 are deleted. Sub-Articles (3) and (5) are re-numbered as Sub-Articles (2) and (3) respectively.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.35

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፭· የአንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፮) ተሰርዘዋል። ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፯) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ሆነዋል።

፮· ከአንቀጽ ፵፱ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፶ እና ፶፩ ተጨምረዋል። የደንቡ አንቀጽ ፶፣ ፶፩፣ እና ፶፪ እንደቅደም ተከተላቸው ፶፪፣ ፶፫፣ እና ፶፬ ሆነዋል።

"፶· <u>በባለሥልጣኑ ስለሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች</u>

ባለሥልጣኑ፤

፩· በአገር አቋራጭ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሠማሩ፤

፪· ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ ወይም የዓለም አቀፍና የተራድኦ ድርጅቶች፣ እና

፫· ንብረትነታቸው የፌዴራል መንግሥት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሔድ፤

አመቺ የሆነ አደረጃጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

"፶፩· <u>ስለ መከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ</u>

፩· የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በዚህ ደንብ መሠረት ለአገር ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር፣ የመታወቂያ ሠሌዳ ቁጥር፣ እና የዓመታዊ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ሊወከል ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ የሚሰጠው የመታወቂያ ሠሌዳ በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ "ለ" ከተመለከተው የቀለም ኅብር፣ የፊደል ጣምራ ወይም ምልክቶች የተለየ መሆን አለበት።"

፯· ሠንጠረዥ "ሀ" እና "ለ" ተሰርዘው ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት አዲስ ሠንጠረዥ "ሀ" እና "ለ" ተተክተዋል።

፰· "የሠሌዳ ሥዕላዊ መልክ" በሚል ርዕስ ከዚህ ደንብ ጋር የተያያዘው አዲስ ሠንጠረዥ "ሐ" ተጨምሯል።

፫· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

5) Sub-Articles (4) and (6) of Article 28 are deleted. Sub-Articles (5) and (7) are re-numbered as Sub-Articles (4) and (5) respectively.

6) The following new Articles 50 and 51 are added and the former Articles 50, 51 and 52 are re-numbered as Articles 52, 53 and 54 respectively.

"50 *Vehicles to be registered by the Authority*

The Authority shall follow the favourable organizational set-up to conduct annual registration and technical inspection to motor vehicles:

1) engaged in cross-country road transport service;
2) owned by diplomatic missions or international organizations; and
3) owned by the Federal Government.

"51 *Defence force vehicle*

1) The Authority may, pursuant to these Regulations, delegate the Minsitry of National Defence, to issue title certificate book, plates, and annual stickers to vehicles owned by the Ministry.
2) Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, plates issued to the National Defence Force vehicles shall be different from the colour and letter combinations specified on schedule "B" of these Regulations.

7. Schedules "A" and "B" are deleted and replaced by new Schedules "A" and "B"

8. A new Schedule "C" attached hereto, with a heading "pictorial representation of plate" is added.

3. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of the date of their pulication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2001.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

# ሠንጠረዥ ሀ

## የአገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | | | የአገልግሎት ዓይነት | ክፍያ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የባለንብረትነት መታወቂያ ሲሰጥ | | | ብር | ሣ |
| | ሀ | | ለሞተር ሳይክሎች | 5 | 00 |
| | ለ | | ሌሎች ተሽከርካሪዎች ሁሉ | 10 | 00 |
| | ሐ | | ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ በያንዳንዱ ጉዳይ | 3 | 00 |
| | መ | | ለባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ግልባጭ ከዋና ክፍያ በተጨማሪ | 3 | 00 |
| | | | | | |
| 2 | የመታወቂያ ቁጥር ሠሌዳ | | | | |
| | ሀ | | የዕለት ሠሌዳ ሲሰጥ ወይም ሲታደስ | 15 | 00 |
| | ለ | | ነዋሪ ሠሌዳ ሲሰጥ ወይም እንደገና ሲሰጥ ለሞተር ሳይክል | 8 | 00 |
| | ሐ | | ነዋሪ ሠሌዳ ሲሰጥ ወይም እንደገና ሲሰጥ ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ሁሉ | 10 | 00 |
| | መ | | ተላላፊ ሠሌዳ ሲሰጥ ወይም ሲታደስ | 30 | 00 |
| | | | | | |
| 3 | ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ፣ ምዝገባና ተለጣፊ ምልክት ሲሰጥ | | | | |
| | 3.1 | | ለሞተር ሳይክሎች | 16 | 00 |
| | 3.2 | | የነጂውን መቀመጫ ጨምሮ የሚከተለውን የወንበር መጠን ላላቸው የግል አውቶሞቢሎችና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ | | |
| | | ሀ | ከአምስት የማይበልጥ መቀመጫ ላላቸው | 41 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 2 | 50 |
| | | ለ | ከ6-44 መቀመጫ | 56 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 3 | 00 |
| | | ሐ | ከ45-64 መቀመጫ | 63 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 3 | 00 |
| | | መ | ከ65 መቀመጫ በላይ | 70 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 3 | 00 |
| | | | | | |
| | 3.3 | | የሚከተለውን የኩንታል ጭነት መጠን ላላቸው ተሽከርካሪዎች | ብር | ሣ |
| | | ሀ | ከ5-70 ኩንታል | 46 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 3 | 00 |
| | | ለ | ከ71-120 ኩንታል | 123 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 2 | 00 |
| | | ሐ | ከ121 ኩንታል በላይ | 200 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 1 | 50 |
| | | መ | ማንኛውም ተሣቢ | 46 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 0 | 75 |
| | 3.4 | | ልዩ ልዩ ተንቀሳ ቃሽ መሣሪያ | 200 | 00 |
| | 3.5 | | ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ በእያንዳንዱ ጉዳይ | 3 | 00 |
| | 3.6 | | ለተለጣፊ የምርመራ ምልክት ግልባጭ | 5 | 00 |
| | 3.7 | | ለዓመታዊ የምዝገባ ካርድ ግልባጭ | 8 | 00 |
| | | | | | |
| 4 | ኦፊሴየል መዝገብን፣ ሠነዶችንና ዝርዝሮችን ለማየት | | | | |
| | ሀ | | ኦፊሴየል መዝገብን፣ ሠነዶችንና ዝርዝሮችን ለመመልከት | 3 | 00 |
| | ለ | | ኦፊሴየል መዝገብ ወይም በሠነዶች ውስጥ የሚገኝ የሪኮርድ ግልባጭ ለመቀበል በአንድ ገጽ፣ | 5 | 00 |
| | ሐ | | ለኦፊሴየል ዝርዝር ግልባጭ በአንድ ገጽ | 3 | 00 |

# SCHEDULEA A
# FEES AND CHARGES

| N.0 | TYPE OF SERVICES | | | | CHARGE | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Issue of Title Certificate Book | | | | Birr | Cents |
| | A | Motor Cycle | | | 5 | 00 |
| | B | All Other Vehicles | | | 10 | 00 |
| | C | Change of Particulars per item | | | 3 | 00 |
| | D | Duplicate Title Certificate Book Original Amount plus | | | 3 | 00 |
| | | | | | | |
| 2 | Identification Number Plates | | | | | |
| | A | Issue or Renewal of Temporary Plates | | | 15 | 00 |
| | B | Issue or Re-issue of Permanent Plates for Motor Cycles | | | 8 | 00 |
| | C | Issue or Re-issue of Permanent Plates for all other Vehicles | | | 10 | 00 |
| | D | Issue or Renewal of Transferable Plates | | | 30 | 00 |
| | | | | | | |
| 3 | Annual Vehicle Inspection, Registration and Issue of Inspection Certificate | | | | | |
| | 3.1 | Motor Cycles | | | 16 | 00 |
| | 3.2 | Private Motor Cars and Public Service Vehicles with the following seating capacity including driver's seat | | | | |
| | | | A | At most 5 seats | 41 | 00 |
| | | | | Plus per seat | 2 | 50 |
| | | | B | 6-44 seats | 56 | 00 |
| | | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | | C | 45-64 seats | 63 | 00 |
| | | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | | D | Above 65 seats | 70 | 00 |
| | | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | | | | | |
| | 3.3 | Trucks with the following load capacity | | | Birr | Cents |
| | | | A | 5 to 70 quintals | 46 | 00 |
| | | | | Plus per quintal | 3 | 00 |
| | | | B | 71-120 quintals. | 123 | 00 |
| | | | | Plus per quintal | 2 | 00 |
| | | | C | Above 121 quintals | 200 | 00 |
| | | | | Plus per quintal | 1 | 50 |
| | | | D | Any trailer | 46 | 00 |
| | | | | Plus per quintal | 0 | 75 |
| | 3.4 | Special Mobile Equipment | | | 200 | 00 |
| | 3.5 | Change of Particular Per Item | | | 3 | 00 |
| | 3.6 | Duplicate of Inspection Certificate | | | 5 | 00 |
| | 3.7 | Duplicate of Annual Registration | | | 8 | 00 |
| | | | | | | |
| 4 | Public Use of Official Register, Records and Lists | | | | | |
| | A | Inspection of Official Register, Record and Lists | | | 3 | 00 |
| | B | Certified Copy of any document or part thereof contained in the Official Register or Records per page | | | 5 | 00 |
| | C | Copy of Official lists Per Page | | | 3 | 00 |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

# SCHEDULEA A
# FEES AND CHARGES

| N.0 | TYPE OF SERVICES | | | CHARGE | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Issue of Title Certificate Book | | | Birr | Cents |
| | A | Motor Cycle | | 5 | 00 |
| | B | All Other Vehicles | | 10 | 00 |
| | C | Change of Particulars per item | | 3 | 00 |
| | D | Duplicate Title Certificate Book Original Amount plus | | 3 | 00 |
| | | | | | |
| 2 | Identification Number Plates | | | | |
| | A | Issue or Renewal of Temporary Plates | | 15 | 00 |
| | B | Issue or Re-issue of Permanent Plates for Motor Cycles | | 8 | 00 |
| | C | Issue or Re-issue of Permanent Plates for all other Vehicles | | 10 | 00 |
| | D | Issue or Renewal of Transferable Plates | | 30 | 00 |
| | | | | | |
| 3 | Annual Vehicle Inspection, Registration and Issue of Inspection Certificate | | | | |
| | 3.1 | Motor Cycles | | 16 | 00 |
| | 3.2 | Private Motor Cars and Public Service Vehicles with the following seating capacity including driver's seat | | | |
| | | A | At most 5 seats | 41 | 00 |
| | | | Plus per seat | 2 | 50 |
| | | B | 6-44 seats | 56 | 00 |
| | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | C | 45-64 seats | 63 | 00 |
| | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | D | Above 65 seats | 70 | 00 |
| | | | Plus per seat | 3 | 00 |
| | | | | | |
| | 3.3 | Trucks with the following load capacity | | Birr | Cents |
| | | A | 5 to 70 quintals | 46 | 00 |
| | | | Plus per quintal | 3 | 00 |
| | | B | 71-120 quintals. | 123 | 00 |
| | | | Plus per quintal | 2 | 00 |
| | | C | Above 121 quintals | 200 | 00 |
| | | | Plus per quintal | 1 | 50 |
| | | D | Any trailer | 46 | 00 |
| | | | Plus per quintal | 0 | 75 |
| | 3.4 | Special Mobile Equipment | | 200 | 00 |
| | 3.5 | Change of Particular Per Item | | 3 | 00 |
| | 3.6 | Duplicate of Inspection Certificate | | 5 | 00 |
| | 3.7 | Duplicate of Annual Registration | | 8 | 00 |
| | | | | | |
| 4 | Public Use of Official Register, Records and Lists | | | | |
| | A | Inspection of Official Register, Record and Lists | | 3 | 00 |
| | B | Certified Copy of any document or part thereof contained in the Official Register or Records per page | | 5 | 00 |
| | C | Copy of Official lists Per Page | | 3 | 00 |
| | | | | | |
| | | | | | |

## ሠንጠረዥ "ለ"

### የባለሞተር ተሽከርካሪና ተሳቢ መታወቂያ ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች

በመታወቂያ ሠሌዳዎች ላይ ያለው የቀለም ኅብር ሠሌዳዎቹ የተለጠፉባቸውን ተሽከርካሪዎች ባለንብረትና የተሰማሩበትን የሥራ መስክ ያመለክታል። የቀለም ሕብሩና ትርጉሙ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ይሆናል።

1. **የታክሲ ሠሌዳ ቀለም ኅብር**

ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል በቀይ ክብ ውስጥ "1" ቁጥር መለያ የተጻፈበት።

**ትርጉም**

በታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለ ሞተር ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ።

2. **የቤት ሠሌዳ ቀለም ኅብር**

ነጭ መደብ ከደማቅ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል በሰማያዊ ክብ ውስጥ "2" ቁጥር መለያ የተጻፈበት።

**ትርጉም**

ለቤት ወይም ለቤተሰብ። አገልግሎት እንዲውሉ ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ።

3. **የንግድ ሠሌዳ የቀለም ኅብር**

ነጭ መደብ ከደማቅ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል በአረንጓዴ ክብ ውስጥ "3" ቁጥር መለያ የተጻፈበት ።

**ትርጉም**

በንግድ የመንገድ ማመላለሻ ለተመዘገቡ ወይም በጉዞ ውክልና ፈቃድ ለሚከራዩ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ ።

4. **የመንግሥት ሠሌዳ የቀለም ኅብር**

ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል በጥቁር ክብ ውስጥ "4" ቁጥር መለያ የተጻፈበት።

**ትርጉም**

ከመከላከያ ኃይል በስተቀር ንብረትነታቸው በንግድ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሆኑት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ።

5. **የሃይማኖት ድርጅቶችና የማህበራት ሠሌዳ ቀለም ኅብር**

ነጭ መደብ ከብርትኳንማ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል ብርትኳንማ ክብ ውስጥ "5"ቁጥር መለያ የተፃፈበት።

**ትርጉም**

ለሃይማኖት ድርጅቶች። ለቀይ መስቀል ነጋዴ ላልሆኑ ማህበራትና ለመሳሰሉት ተቋማት አገልግሎት እንዲውሉ ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ።

## SCHEDULE B

### Motor Vehicle And Trailer Identification Plate, Types and Symbols

Colour combinations used on plates shall identify the ownership and use of the vehicles. The following colour combinations shall have meanings prescribed below.

1. TAXI PLATE

| COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with red letters and numerals with code number "1" in a red circle on the left hand side. | Issued to vehicles engaged in taxi transport service. |

2. PRIVATE PLATE

| COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with dark blue letters and numerals with code number "2" in a blue circle on the left hand side. | Issued to private motor cars used for personal and family purposes. |

3. COMMERCIAL PLATE

| COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with dark green letters and numerals with code number "3" in a green circle on the left hand side. | Issued to vehicles, registered for commercial road transport use and car hire operating licence. |

4. GOVERNMENT PLATE

| COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with black letters and numerals with code number " 4" in a black circle on the left hand side. | With the exception of the National Defence Forces issued to vehicles on by the Federal or Regional Government Agencies not engaged in commerce. |

5. RELIGIOUS & CIVIC SOCIETIES

| PLATE COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with orange letters and nuemerals with code number "5" in an orange circle on the left hand side. | Issued to motor vehicless owned by Red cross, religious societies, non business associations and similar other institutions. |

| | |
|---|---|
| 6. **የጊዜያዊ ሠሌዳ የቀለም ኅብር** | **ትርጉም** |
| ሀ. ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል "የዕለት" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ሀ. ለማንኛውም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ በጊዜያዊነት የሚሰጥ። |
| ለ. ነጭ መደብ ከደብዛዛ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል "ተላላፊ" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ለ. ለማንኛውም አይነት ባለ ሞተር ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ ለፍተሻ ከወደብና ከጉምሩክ ለማስወጣትና ለማስገባት ሽያጭ ቦታ ለማድረ ስና ለመሳሰሉት በጊዜያዊነት የሚሰጥ። |
| 7. **የልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ሠሌዳ ቀለም ኅብር** | **ትርጉም** |
| ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል "ልዩተ" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ለማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የሚሰጥ። |
| 8. **የፖሊስ ሠሌዳ የቀለም ኅብር** | **ትርጉም** |
| በብጫ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራ ክንፍ በኩል "ፖሊስ" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ንብረትነታቸው የፖሊስ ለሆኑ ተሽ ከርካሪዎች የሚሰጥ። |
| 9. **የኤምባሲዎች፣የአለም አቀፍና የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ሠሌዳ የቀለም ኅብር** | **ትርጉም** |
| ሀ. ነጭ መደብ ከደብዛዛ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ ቢጫ ቀለም ላይ "ኮዲ"፣ "የተመ"፣ "UN" እና "CD" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ሀ. በተባበሩት መንግስታት መ/ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለስልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |
| ለ. ነጭ መደብ ከደብዛዛ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ "የተመ" እና "UN" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ለ. ለተባበሩት መንግሥታት መሥሪያ ቤት ወይም ለመሥሪያ ቤቱ አባላት ተሽከርከሪዎች የሚሰጥ። |
| ሐ. ነጭ መደብ ከደብዛዛ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ ቢጫ ቀለም ላይ "ኮዲ"፣ "አአድ"፣ "OAU" እና "CD" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ሐ. በአፍሪካ አንድነት ድርጅት መ/ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለስልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |

| 6. TEMPORARY PLATE COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| | Issued to:- |
| A. White ground with red letters and numerals with the legend "የዕለት" on the left hand side. | A. any motor vehicle or trailer for temporary use. |
| B. White ground with light blue letters and numerals with the legend "ተላላፊ" on the left hand side. | B. to any motor vehicle or trailer for the purpose of testing, customs clearance, transfering to display area and the like for temporary use. |

| 7. SPECIAL MOBILE EQUIPMENT PLATE COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| White ground with red letters and numerals with legend "ልዩ·ተ" on the left hand side. | Issued to any special mobile equipment. |

| 8. POLICE PLATE COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| Yellow ground with black letters and numerals with the legend "ፖሊስ" on the left hand side. | Issued to vehicles owned by the police. |

| 9. EMBASSY, INTERNATIONAL ORGANIZATIONS AND AID PLATE COLOUR COMBINATION | MEANING |
|---|---|
| | Issued to:- |
| A. White ground with light blue letters and numerals with letter combination "ኮዲ", "የተመ", "UN" and "CD" on yellow stripes on the left and right handside. | A. Vehicles of "UN" Personnel with diplomatic status. |
| B. White ground with light blue letters and numerals with letter combination "የተመ" and "UN" on the left and right hand sides. | B. Vehicles owned by "UN" and the personnel thereof. |
| C. White ground with light green letters and numerals with letter combination "ኮዲ", "አአድ", "OAU" and "CD" on the left and right hand sides. | C. Vehicles of OAU personnel with diplomatic status. |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መ. | ነጭ መደብ ከደብዛዛ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ከንፍ "እአድ" እና "OAU" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | መ. | ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስሪያ ቤት ወይም ለድርጅቱ አባላት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |
| ሠ. | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በመሃልና ቀኝ ክንፍ በቢጫ ቀለም ላይ "ኮዲ" እና "CD" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ሠ. | ለዲፕሎማቲክ መልእክተኞች ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |
| ረ. | ነጭ መደብ ከብርቱካንግ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ "ኮዲ" እና "CD" የሚል ጽሑፍ የሚገኝበት። | ረ. | በተራድኦ ድርጅት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለሥልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |
| ሰ. | ነጭ መደብ ከብርቱካንግ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር። | ሰ. | ለተራድኦ ድርጅቶችና በዕርዳታ ለሚመጡ ባለሙያዎችና ግለሰቦች ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ። |

10. <u>በሠሌዳዎች ላይ የሚታዩ የፊደል ጣምራዎች</u>

<u>ሀ</u>

የሚከተሉት የፊደል ጣምራ ያለባቸው ሠሌዳዎች የተለጠፉባቸው ተሽከርካሪዎች የተመዘገቡበትን ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ሠሌዳ ያመለክታል።

| | የፊደል ጣምራዎች | | ክልል መስተዳድር |
|---|---|---|---|
| 1. | አአ | AA | የአዲስ አበባ መስተዳድር |
| 2. | አፋ | AF | የአፋር ክልል |
| 3. | አማ | AM | የአማራ ክልል |
| 4. | ቤጉ | BG | የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል |
| 5. | ድሬ | DR | የድሬዳዋ መስተዳድር |
| 6. | ጋም | GM | የጋምቤላ ክልል |
| 7. | ሐረ | HA | የሐረሪ ሕዝብ ክልል |
| 8. | ኦሮ | OR | የኦሮሚያ ክልል |
| 9. | ሱማ | SM | የሱማሌ ክልል |
| 10. | ደሕ | SP | የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል |
| 11. | ትግ | TG | የትግራይ ክልል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| D. | White ground with light green letters and numerals with letter combinations "ኦአድ " and "OAU" on the left and right hand sides. | D. | Vehicles owned by the OAU and the personnel thereof. |
| E. | White Ground with Black letter and numerals with letter combination "ኮዲ" and "CD" on yellow stripes at the center and right hand side. | E. | Vehicles of diplomatic corps. |
| F. | white ground with light orange letters and with letter combination numerals with letter combination "ኮዲ" and "CD" on the left and right hand sides. | F. | Vehicles of aid institutions personnel with dipolmatic status. |
| G. | white ground with orange letters and numerials. | G. | Vehicle of aid institutions and personnel. |

10. LETTER COMBINATIONS

A. The following letter combinations indicate the state where the vehicle is registered in.

| LETTER COMBINATIONS | | | STATES |
|---|---|---|---|
| 1/ | አአ | AA | Addis Ababa Administration |
| 2/ | አፋ | AF | The State of Afar. |
| 3/ | አማ | AM | The State of Amhara |
| 4/ | ቤጉ | BG | The State of Benshangual Gumz |
| 5/ | ድሬ | DR | Dire Dawa Administration |
| 6/ | ጋም | GM | The State of Gambella |
| 7/ | ሐረ | HA | The State of Harari People |
| 8/ | ኦሮ | OR | The State of Oromia |
| 9/ | ሶማ | SM | The State of Somalia |
| 10/ | ደሕ | SP | The State of Southern Nations, Nationalities & Peoples. |
| 11/ | ትግ | TG | The state of Tigray |

**ለ**

| | | |
|---|---|---|
| ኢ.ት | ETH | ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሚያገናኝ የንግድ የመንገድ ማመሏለሻ ሥራ የሚሰራ ወይም ንብረትነቱ የማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት የሆነ ተሽከርካሪ። |

11. **ሌሎች ምልክቶች**

በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት የቀለም ኅብርና የፊደል ጣምራዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ የሠሌዳ ዓይነት ሌዘር ኮድ፣ ሆሎግራም እና በቀላሉ የማይታይ ምልክት ይኖረዋል።

B.

| | |
|---|---|
| ኢ.ት ETH | A vehicle engaged in cross country commercial road transport service or owned by any Federal Government Institution. |

11 OTHER FEATURES

Subject to the colour and letter combinations stated herein these regulations each type of plate shall have laser code, hologram and water marking.

ሠንጠረዥ "ሐ"
የሰሌዳ ስዕላዊ መልክ

SCHEDULE C
PICTORIAL REPRESENTATION OF PLATE



